## ትምህርት 5

**እግዚአብሔር በኃጢአት ለወደቀው የሰው ዘር የተስፋ ቃልና የስራ ሕግ መስጠቱ**

እግዚአብሔር በኃጢአት ለወደቀው የሰው ዘር ወደ ክብር ለመመለስ የተስፋ ቃል ሰጠ፡ -

እግዚአብሔር መጀመሪያ ላይ ሆኖ ወደፊት መጨረሻ ላይ የሰው ዘር አካሄድ ምን ዓይነት በኃጢዓት የተበከለ እንደሚሆን ያውቅ ስለነበር የሰው ዘር በገዛ ራሱ ኃጢአት ምክንያት ምን ዓይነት አስከፊና አስጨናቂ ውጤት እንደ ሚጠብቀው ዓይቶ ስለራራ የሚድኑበት መንገድ እንደ ሚከፍትላቸው የተስፋ ቃል ሰጠ፡፡ የተስፋ ቃሉም ፍሬ ነገር በአጭሩ እግዚአብሔር በኃጢአት የተበከለው የሰው ዘርን ለማዳን በሚልከው አዳኝ የሚፈጸመው የጽድቅ ስራ የሰውን ዘር ከኃጢአቱ ውጤት ሁሉ ነጻ ያወጣል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ ያለ ማንም አስገዳጅነት ይህን አዳኝ ሲመጣ የሚናገረውን አምነው ከተቀበሉ አስተምህሮውን ተከትለው ከኖሩ ኃጢአታቸው ሁሉ ከሚያስከትልባቸው እርግማንና የዘላለም ሞት እንዲድኑ የሚያስችል ነው፡፡

አዳኝ እንደሚመጣ ከተሰጡ እጅግ በርካታ የተስፋ ቃሎች መካከል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡ -

**ዘፍጥረት** 3፡15፣ "በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘሯ መካከል፣ ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅጣለህ።"

**ኢሳይያስ** 28፥16፣ "ስለዚህ ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "እነሆ፤ የተፈተነ ድንጋይ፣ የመሠረት ድንጋይ፣ ለጽኑ መሠረት የሚሆን የከበረ የማእዘን ድንጋይ፣ በጽዮን አስቀምጣለሁ፤ በእርሱም የሚያምን አያፍርም።"

**ኢሳይያስ** 61፡1-2፣ የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች የምሥራች እንድሰብክ፣ እግዚአብሔር ቀብቶኛል። ልባቸው የተሰበረውን እንድጠግን፣ ለምርኮኞች ነጻነትን፣ ለእስረኞች መፈታትን እንዳውጅ ልኮኛል፤

2 የተወደደውን የእግዚአብሔርን ዓመት፣ የአምላካችንንም የበቀል ቀን እንዳውጅ፣ የሚያለቅሱትን ሁሉ እንዳጽናና ልኮኛል፤

**ኢሳይያስ** 59፥20፣ "አዳኝ ወደ ጽዮን፣ ኀጢአታቸውንም ወደ ተናዘዙት ወደ ያዕቆብ ቤት ይመጣል" ይላል እግዚአብሔር።"

**ኢሳይያስ** 53፡1-9፣ "የሰማነውን ነገር ማን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ? 2 በፊቱ
እንደ ቡቃያ፣ ከደረቅም መሬት እንደ ወጣ ሥር በቀለ፤ የሚስብ ውበት ወይም ግርማ የለውም፤
እንድንወደውም የሚያደርግ መልክ አልነበረውም። 3 በሰዎች የተናቀና የተጠላ፣ የሕማም ሰውና
ሥቃይ ያልተለየው ነበር። ሰዎች ፊታቸውን እንደሚያዞሩበት ዐይነት፣ የተናቀ ነበር፤ እኛም
አላከበርነውም። 4 በርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን
በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው። 5 ነገር ግን እርሱ ስለ
መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም
አመጣልን፤ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። 6 እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤
እያንዳንዳችንም በየመንገዳችን ነጐድን፤ እግዚአብሔርም፣ የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ጫነው። 7
ተጨነቀ፤ ተሠቃየም፤ ነገር ግን አፉን አልከፈተም፤ እንደ ጠቦትም ለዕርድ ተነዳ፤ በሸላቾች ፊት
ዝም እንደሚል በግ፣ አፉን አልከፈተም። 8 በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኀጢአት

*ተመቶ፣ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ፣ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? [9] በአፉ ተንኰል ሳይገኝበት፣ ምንም ወንጀል ሳይሠራ፣ አሟሟቱ ከክፉዎች፣ መቃብሩም ከባለጠጎች ጋር ሆነ።”*

በተጨማሪ **ኢሳያስ** 42፡1-8 ማንበብ ይቻላል፡፡

***የሰው ዘር በኃጢአት ምክንያት ከነበረበት መንፈሳዊ ከፍታ ከወደቀ በኋላ እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ሕጎችን ለሰው ሰጠ፡፡*** እነርሱም፡ -

1. ***የብሉይ (የአሮጌ) ኪዳን ወይም የሥራ ሕግ፡-*** በተለይም ለእስራኤላዊያን እርስ በራሳቸውና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ያማረ እንዲሆን ማድረግ የሚገባቸውን፣ እግዚአብሔር የሚወዳቸው (የሚፈቅዳቸው) መልካም ተግባራትና ማድረግ የማይገባቸው ክፉ (የተከለከሉ) ተግባራት በመዘርዘር የአኗኗር ሕግ ሰጥቷል፡፡ ይህም ህግ በብሉይ ኪዳን መጻህፍት ሰፍሮ ያለ ነው፡፡ ሕግጋቱም የስነ-ምግባር (ሞራል)፣ የክብረ-በዓላትና የአምልኮ ሥርዓት (ሴሬሞኒያል) እንዲሁም የፍትሐብሔር (ሲቪል/ጁዲሺያል) ሕግጋት ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ እነዚያን ሕግጋት ሙሉ በሙሉ ከጠበቁ እግዚአብሔር በእነርሱ ደስ እንደሚሰኝና በተለያዩ ምድራዊና መንፈሳዊ በረከቶች እንደሚባርካቸው ተናገራቸው፡፡ እነዚያን ሕግጋት ባለመፈጸም ካልታዘዙት /ካመጹበት/ የሚደርስባቸው ብዙ ቅጣቶችና መርገም ዓይነት ዘርዝሮ አሳወቃቸው፡፡
2. የህሊና ሕግ፡- ይህ ሕግ በዓለም ውስጥ ለሚኖሩት ከእስራኤል ዘር ውጪ ለሆኑት ሕዝቦች ሁሉ መስጠቱ የእግዚአብሔር ቃል ይገልጻል፡፡ ይህ ህግ በጽሁፍ የሰፈረ ሳይሆን በእያንዳንዱ ሰው ህሊና ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠው ክፉና ደጉን ለይቶ እንዲያውቅ የሚያስችል ሕግ ነበር፡፡
   ሮሜ 2፡14፣15፣ ***“ሕግ የሌላቸው አህዛብ ሕግ የሚያዘውን ነገር በተፈጥሮ ሲያደርጉ፣ ሕግ ባይኖራቸውም እነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው፡፡ ሕሊናቸው ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣ ደግሞም ስለሚከለክላቸው የሕግ ትዕዛዝ በህሊናቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያሉ፡፡”*** ይላል፡፡

*ነገር ግን እነዚህን ሕግጋት ሙሉ በሙሉ በምድር በኖረበት ዘመን ሁሉ ኃጢአት ሳይቀላቅል መጠበቅ/መፈጸም የቻለ ሰው እግዚአብሔር አንድም አላገኘሁም አለ፡፡*

*መዝ* 14፡1-3፣ "***ሞኝ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል፡፡ ብልሹዎች ናቸው፣ ተግባራቸው ጸያፍ ነው፣ በጎ ነገር የሚሰራ አንድም የለም፡፡ የሚያስተውል እግዚአብሔርን የሚፈልግ መኖሩን ለማየት እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ፡፡ ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፣ በአንድ ላይ ብልሹ ሆነዋል፤ አንድ እንኳ መልካም የሚያደርግ የለም***፡፡"

**ሮሜ** 3፡10-19፣ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ “ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤ [11] አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም። [12] ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ።” [13] “ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤ አንደበታቸው ሽንገላን ያዘወትራል።” “በከንፈሮቻቸው የእባብ መርዝ አለ።” [14] “አፋቸው ርግማንና ምሬት ሞልቶበታል።” [15] “እግራቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣን ነው፤ [16] በመንገዳቸው ጥፋትና ጕስቍልና ይገኛል፤ [17] የሰላምንም መንገድ አያውቁም።” [18] “በዐይናቸው ፊት የእግዚአብሔር ፍርሀት የለም።”

**ሮሜ** 3፥20 “ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም፤ ይልቁንም በሕግ አማካይነት ኀጢአትን እንገነዘባለን።”

ማንኛውም ሰው ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቅ አይችልም የተባለበት ምክንያት አንድ ሰው ኃጢአት የሌለበት ፍጹም ጻድቅ መባል የሚችለው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕግጋት ሁሉ ምንም ሳያጎድል መፈጸም ከቻለ ነውና፡፡

የብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ ሰው ሁሉ አንድም ሳይቀር ኃጢአተኛ መሆኑና ማንም ቢሆን እድሜ ልኩን ምንም ኃጢአት ሳይሰራ በምድር መኖር የቻለ እንደሌለ አረጋግጠው ይናገራሉ፡፡ ይህ ማለት ግን አንዱ ሰው ከሌላው የተሻለ የጽድቅ ሥራ አልነበረውም (አይኖረውም) ማለት አይደለም፡፡ ቀጥሎ የተመለከቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይህን ዕውነት ያረጋግጣሉ፡፡

ዘዳ 15:4-5, ይሁን እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ትወርሳት ዘንድ ርስት አድርጎ በሚሰጥህ ምድር ውስጥ አብዝቶ ስለሚባርክህ፣ በመካከልህ ድኻ አይኖርም፤ [5] ይህ የሚሆነውም ለአምላክህ ለእግዚአብሔር (ኤሎሂም ያህዌ) ፈጽመህ ስትታዘዝና ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዞች ሁሉ በጥንቃቄ ስትከተል ብቻ ነው። (ዘዳ 28፡15)

**ገላ** 3፡10፣ 11፣ "ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ ከእርግማን በታች ናቸውና፤ በህግ መጻሕፍት የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ስለተባለ፣ ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደ ማይጸድቅ ግልጽ ነው፡፡"

**ያዕቆብ** 2፡10-11፣ ምክንያቱም ሕግን ሁሉ የሚፈጽም ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ቢኖር፣ ሁሉን እንደ ተላለፈ ይቈጠራል። [11] “አታመንዝር” ያለ እርሱ ራሱ “አትግደልም” ብሎአልና። ባታመነዝር፣ ነገር ግን ብትገድል፣ ሕግ ተላላፊ ሆነሃል።

የብሉይ ኪዳን ህግም ሆነ የህሊና ህግ ከተሰጣቸው ሰዎች መካከል የተለያየ መልካም ስራ የሰሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ ከሰሩት ክፉ ስራ ይልቅ የሰሩት መልካም ስራ ሊበልጥ ይችላል፡፡ ነገር ግን የሰሩት መልካም ስራ ስለበለጠ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ጻድቅ አያሰኛቸውም፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የሚያሰኘው በምድር በኖሩበት ዘመን ሁሉ እግዚአብሔር አድርጉ ያላቸውን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ካደረጉ ብቻ ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን የተሰጡት ሕግጋትም ብዛት 613 ነበር፡፡

ታዲያ እግዚአብሔር ሕግን ለሰው ሲሰጥ ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቅ የሚችል ሰው እንደማይኖር አላወቀም ወይ፣ ካወቀስ ለምን ሕግ ሰጠ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚያውቅ ሕግን ቢሰጥም ሰው ሙሉ በሙሉ ሊጠብቀው እንደማይችል ያውቅ ነበር፡፡ ሕግን የሰጠው እያንዳንዱ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እንዲያውቅና በራሴ ብርታት በመልካም ስራዬ በእግዚአብሔር ፊት ጸድቄያለሁ ማለት የሚደፍርና በራሱ የሚመካ ማንም እንዳይኖርና ሁሉም በጌታ በኢየሱስ የማዳን ስራ ብቻ እንዲመካ ነው፡፡

ሕግ የተሰጠበት ሌላው ምክንያት ማንም ሰው በራሱ ጥረትና ብርታት መልካም ስራ በመስራት ፍጹም ሆኖ የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ በጭራሽ እንደማይችል ተረድቶ, እግዚአብሔር ሰጥቶ በነበረው የተስፋ ቃል መሰረት በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰራለትን የማዳን ስራ በእምነት በመቀበል ወደ መዳን እንዲደርስ መሆኑን ቀጥሎ የሰፈሩት ጥቅሶች ያስረዳሉ፡፡

ሮሜ 3፡19፣ 20፣ *እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም ሁሉ ለእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ እግዚአብሔር የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም፣ ይልቁን በህግ አማካይነት ኃጢአት እንገነዘባለን፤* ይላል፡፡

ገላ 3፡24፣ *ስለዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያደርስ ሞግዚታችን ሆነ፡፡*

በዚህ ምክንያት ጽድቅ በሁለት መንገድ ይመጣል ማለት ነው፡-

1. **በሥራ የሚገኝ ጽደቅ፡-** እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጣቸውን ትዕዛዛት ሁሉ አንድም ሳይቀር በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በየዕለቱ አንድም ኃጢአት ሳይቀላቅሉ ከፈጸሙ የሚገኝ ጽድቅ ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ፅድቅ ማግኘት የቻለ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ማንም ስጋ ለባሽ ሰው አልተገኘም (አልቻለም)፡፡ ኢሳ 64፡6፤ ሮሜ 3፡10-12
2. **በእምነት የሚገኝ ጽድቅ፡-** ሮሜ 4፡3 "አብርሐም እግዚአብሔርን አመነ፣ ስለዚህ (እምነቱ) ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት"፣ እንደሚል በዚህ ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ መስቀል ሞት ድረስ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የፈጸመው መልካም ስራ ለእኔ ጽድቅ ሆኖ እንዲቆጠር ነው፣ ብሎ የሚያምን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል፡፡ ይሄ የእግዚአብሔር የጽድቅ ስጦታ በእምነት በመቀበል የሚገኝ ነው፡፡ ሮሜ 3፡21-23፣ ገላ 2፡ 16፡፡

በዚህ ዘመን የአንዳንድ ሃይማኖት አስተማሪዎች ሰው የዘላለም ሕይወት ማግኘት የሚያስችል መልካም ስራ በእግዚአብሔር ፊት በመስራት ሊጸድቅና የዘላለም ሕይወት ሊወርስ ይችላል ብለው የሚያስተምሩ ሃይማኖቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ይህ አስተምህሮ ከአዲስ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር ይቃረናል፡፡ ሰው በራሱ ስራ ፍጹም መሆን ከቻለ ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ያን ያህል አሰቃቂ ስቃይ ተቀብሎ የሞተው እንዲያው በከንቱ ነው ማለት ይሆናልና፡፡

ይህ ማለት ግን ኃጢአተኛ ሰው በቀደመው ኃጢአቱ ተጸጽቶ ንስሃ በመግባት በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ የኃጢአት ይቅርታ አግኝቶ ከዳነ በኋላ እንደ ፈለገው ኃጢአት በማድረግ መቀጠል አለበት ማለት ሳይሆን፤ ቀድሞ ያደርገው የነበረውን ኃጢአት ማድረግ ትቶ በጌታ ኢየሱስ ያለው እምነት እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት መልካም ማድረግን ከእግዚአብሔር ቃል እየተማረ በቀሪው ዕድሜው ሁሉ ከሰይጣን የሆነውን ኃጢአት እየተወ በመልካም ፍሬ እያደገ መሄድ እንዳለበት የእግዚአብሔር ቃል ያሳያል፡፡ ከዳነ በኋላ የሚሰራው መልካም ስራ አማኙ በእውነት በጌታ ኢየሱስ ያመነና ጌታን የሚወድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ውጫዊ ማስረጃ ሲሆን በወዲያኛውም ዓለም በሰራው መልካም ስራ መጠን ከእግዚአብሔር ዘንድ ሽልማት የሚቀበል ይሆናል፡፡